# *<u>በሶማልያ ያሉ የኢታዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ከፍተኛ አመራሮች በአዲስ አበባ በስብሰባላይ መሆናቸው ተገለፀ፡፡</u>*

እንደ ምንጮቻችን ገለፃ ስብሰባው ካለፈው ሰኞ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ እየተካሄደ ነው፡፡ የስብሰባው ዋንኛ አጀንዳ እንዴት ከሱማልያ ለቀን መውጣት እንችላለን የሚል እንደሆነ እነዚሁ ምንጮቻችን ገልዋል፡፡ የሰራዊቱ አመራር አባላት ኢትዮጵያ በሱማልያ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈለች ነው፣ የታሰበውን መረጋጋት ማምጣት አትችልም፣ ስማችን በተለያዩ ሚዲያዎች እየተበከለ ነው የሚል ሀሳብ ማንሰታቸውን እነዚሁ ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

የስብሰባው ተካፋይ የሆኑ የሰራዊቱ የአመራር አባላት ወደ ስብሰባው አዳራሽ ሲገቡ ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን አስቀምጠው እንዲገቡ  እየተደረገ መሆኑን የገለፁት ምንጮቻችን ይህም የስብሰባውን ሂደት ለሌላ ወገን እንዳያስተላልፉ እና የድምፅም ሆነ የምስል ቅጂዎች ሾልከው ይወጣሉ በሚል ስጋት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከአራት ወራት በፊት ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ የፓርላማ አባላት በሱማልያ ጉዳይ ላይ ላቀረቡላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣‹‹ ሰራዊታችን ለጫጉላ ሽርሽር ሳይሆን ለውጊያ በመሄዱ መጠነኛ ዋጋ ከፍለናል፡፡ ነገር ግን ሰራዊቱ እዚህ ቢቀመጥ ከሚወጣው ወጪ ያልበለጠ ዋጋ ነው የሚያስወጣን፣ በህይወት በኩልም ይህ ነው የሚባል መስዋእትነት አልከፈልንም›› ማለታቸው አይዘነጋም፡፡ ጠ/ሚ መለስ በዚሁ የሸንጎ ስብሰባ ላይ እየከፈልን ያለነው ዋጋ ተመጣጣኝ ነው ይበሉ እንጂ ለአፍሪካ ህብረት እና ለተባበሩት መንግስታት ሸክሙን አልቻልነውም፣ እየከበደን ነው ብለናቸዋል ሲሉ ሁለት ቃል መናገራቸው አይዘነጋም፡፡

የኢትዮጵያ ሰራዊት በሶማልያ ከገባ ከሁለት አመት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም የታሰበውን መረጋጋት ማምጣት አልቻለም፡፡ የሽግግር መንግስቱ የተለያዩ ሚንስትሮችም በገዛ ፍቃዳቸው ሥልጣንቸውን ለቀው እየወጡ ሲሆን ሰሞኑን 10 ሚንስትሮች ከጠቅላይ ሚንስተሩ ጋር መስራት አልቻልንም፣ ከሰባት ወር በላይ ጥቅማ ጥቅም አልተሰጠንም በማለት ሥልጣን መልቀቃቸው ይፋ ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡